ማስተባበያ፡- ይህ መረጃ ለትምህርታዊ ዓላማዎች ብቻ ነው እና የህግ ምክርን አያካትትም። የመጀመሪያ ማሻሻያ ህግ ትግበራ ውስብስብ እና እንደሁኔታው ተለዋዋጭ ሊሆን ይችላል። በእርስዎ ልዩ ሁኔታ መሠረት ምክር ለማግኘት፣ እባክዎ ጠበቃ ያማክሩ።

# <u>መብቶችዎን ይወቁ፡- Virginia ውስጥ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረግ</u>

**እንዴት መቃወም እችላለሁ?**

በሰላም የመቃወም መብት በU.S. እና በVirginia ሕገ-መንግሥታት የተጠበቀ ነው - ነገር ግን የፖሊስ እና የመንግሥት ኃላፊዎች በተቃውሞ ወቅት በሚደረጉ የንግግር መብቶች አጠቃቀም ላይ የተወሰኑ ጠባብ ገደቦችን እንዲተገብሩ ይፈቀድላቸዋል።

**ፖሊስ ንግግሬ አከራካሪ ስለሆነ ሊገድበው ይችላል?**

አይ። የመጀመሪያው ማሻሻያ የእርስዎ ሃሳብ ብዙዎች የሚስማሙበት ባይሆንም እንኳን የመግለጽ መብትዎን ይጠብቃል። ነገር ግን ጥበቃ የማይደረግላቸው ልዩ ሁኔታዎች አሉ፣ ለምሳሌ የስም ማጥፋት ወይም ለጥቃት የሚጋብዝ ንግግር። መንግሥት በንግግር ላይ የሚጥላቸው ማናቸውም ገደቦች አድልዎ የሌለባቸው እና “ጊዜ፣ ቦታ እና ሥርዓትን” ብቻ መሠረት ያደረጉ ጠባብ ገደቦች መሆን አለባቸው።

**አንድ ተናጋሪ ሕዝብን በማነሳሳቱ ምክንያት ዝም እንዲል ሊደረግ ይችላል?**

በአጠቃላይ አይችልም። ታዳሚውን በማነሳሳት ሊቀጡ አይችሉም። ይሁን እንጂ፣ አንድ ተናጋሪ ሕገ-ወጥ ድርጊቶች እንዲፈጸሙ በግልጽ ከቀሰቀሰ እና እነዚያ ሕገ-ወጥ ድርጊቶች ወዲያውኑ የመከሰት ዕድላቸው ከፍተኛ ከሆነ በማነሳሳት ወንጀል ሊፈረድበት ይችላል።

**ተቃውሞ ማድረግ የምችለው የት ነው?**

የመጀመሪያው ማሻሻያ ራስዎን በየትኛው ቦታ በተሻለ መግለጽ እንደሚችሉ የመወሰን መብት ይሰጥዎታል፣ ነገር ግን በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ገደቦች ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ሕገ-መንግስታዊ ጥበቃዎች እንደ የእግረኛ መንገድ ባሉ የሕዝብ ቦታዎች ላይ በጣም ጠንካራ ሲሆኑ በግል ይዞታዎች ላይ ደግሞ በጣም ደካማ ናቸው።

**የተቃውሞ ሰልፍ ማደራጀት እፈልጋለሁ። ፈቃድ ያስፈልገኛል?**

አንዳንድ ጊዜ። ወደ አደባባይ ከመውጣትዎ በፊት የአካባቢዎን የፈቃድ ደንብ ያረጋግጡ።

**ምን ያህል ድምጽ ማሰማት እችላለሁ?**

መልሱ እንደ አካባቢው ሁኔታ እና ንግግር እንደሚያደርጉበት ጊዜ እና ቦታ ይለያያል። የአካባቢዎን ደንቦች ያረጋግጡ።

**በተቃውሞዬ ላይ ተቃራኒ ሰልፈኞች ቢመጡስ?**

ተቃራኒ ሰልፈኞች በነጻነት የመናገር መብት አላቸው እና አብዛኛውን ጊዜ ተቃውሟቸውን እንዲገልጹ ሊፈቀድላቸው ይገባል። ነገር ግን ዝግጅቱን በአካል ማደናቀፍ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ማድረስ የለባቸውም።

**በተቃውሞ ሰልፍ ላይ የፖሊስ ቪዲዮ ወይም ፎቶ ማንሳት እችላለሁ?**

አዎ፣ በአጠቃላይ ይቻላል። በሕዝባዊ ቦታዎች ላይ በግልጽ የሚታይ ማንኛውንም ነገር የመቅረጽ መብት አለዎት። ቀረጻውን በግልጽ ያከናውኑ እና ደህንነቱ በተጠበቀ ርቀት ላይ ይቆዩ። የፖሊስ መኮንን የሕግ ማስከበር ተግባራትን አያግዱ ወይም ጣልቃ አይግቡ። የፖሊስ መኮንኖች በሕዝባዊ ቦታዎች ላይ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ፎቶ የማንሳት፣ ቪዲዮ እና ድምጽ የመቅዳት መብት አለዎት። እንዲሁም የሕዝብ ንግግሮችን ወይም የተቃውሞ ንግግሮችን የሚያደርጉ ሰዎችን መቅረጽ ይችላሉ። ፖሊስ ያለእርስዎ ፈቃድ ፎቶዎችዎን ወይም ቪዲዮዎችዎን *በፍጹምሊያጠፉ* አይችልም። እንዲሁም ያለእርስዎ ፈቃድ ወይም ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የቀረጹትን ምስል ሊቀሙ ወይም እንዲያሳዩዋቸው ሊጠይቁ አይችሉም።

በግል ይዞታ ላይ፣ የፎቶግራፍ ወይም ቀረጻ ደንቦችን የሚወስነው የንብረቱ ባለቤት ነው።

**በተቃውሞ ሰልፍ ወቅት ፊቴ ላይ ጭምብል ማድረግ እችላለሁ?**

በVirginia ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በላይ የሆኑ አብዛኛዎቹ ሰዎች ማንነታቸውን ለመደበቅ በማሰብ ጭንብል ወይም ሌላ የፊት መሸፈኛ ማድረግ በሕግ የተከለከለ ነው። ለተቃውሞ ሰልፍ ምንም ዓይነት ልዩ ሁኔታ የለም።

**ፖሊስ የተቃውሞ ሰልፍን መበተን ይችላል?**

ሊበትን የሚችለው ግልጽ እና አሁን ያለ የጥቃት፣ ግርግር፣ የትራፊክ ፍሰት መስተጓጎል ወይም ሌላ አስቸኳይ የሕዝብ ደህንነት ስጋት ሲኖር ብቻ ነው። የመበተኛ ትዕዛዝ መስጠት የፖሊስ የመጨረሻ አማራጭ መሆን አለበት።

**በተቃውሞ ሰልፍ ላይ ከተያዝኩ ወይም በቁጥጥር ስር ከዋልኩ ምን ይከሰታል?**

ለመረጋጋት ይሞክሩ እና ለፖሊስ መኮንን በፍጹም በአካል አይታገሉ። እጆችዎ በግልጽ እንዲታዩ ያድርጉ። ፖሊሶች መብትዎን እየጣሱ እንደሆነ ቢያምኑ እንኳን አይከራከሩ፣ አይቃወሙ ወይም አያግዷቸው።

በፖሊስ መኮንን እንዲቆሙ ከተደረጉ፣ መሄድ እንደሚችሉ ይጠይቋቸው። መልሱ አዎ ከሆነ፣ በእርጋታ ይራመዱ። ከታያዙ፣ ምን ዓይነት ወንጀል በመፈጸም እንደተጠረጠሩ መኮንኑን ይጠይቁ። በቁጥጥር ስር ከዋሉ፣ ዝም የማለት መብትዎን መጠቀም እንደሚፈልጉ ይናገሩ እና ወዲያውኑ ጠበቃ እንዲመጣልዎ ይጠይቁ። ጠበቃ በሌለበት ምንም ነገር አይናገሩ ወይም በማንኛውም ሰነድ ላይ አይፈርሙ።

መኮንኑ ስልክዎን ወይም ካሜራዎን እንዲመለከቱ ወይም ማንኛውንም ነገር እንዲያጠፉ ፈቃድዎን አይስጡ። ነገር ግን መኮንኑ ስልክዎን ወይም ካሜራዎን ለመውሰድ እጃቸውን ከዘረጉ፣ አይከላከሉ። ለማንኛውም ዓይነት ፍተሻ ወይም ንብረት መውሰድ ፈቃደኛ አለመሆንዎን ብቻ ደጋግመው ይናገሩ።

**በተቃውሞ ሰልፍ ላይ መብቴ ተጥሷል ብዬ ካሰብኩ ምን ማድረግ አለብኝ?**

የሚያስታውሱትን ነገር ሁሉ በዝርዝር ይጻፉ። ከምስክሮች የእውቂያ መረጃን ለማግኘት ይሞክሩ። ማንኛውም ዓይነት የአካል ጉዳት ካለ ፎቶ ያንሱ። በዚህ መረጃ መሠረት፣ ለኤጀንሲው የውስጥ ጉዳይ ክፍል፣ ለአካባቢዎ የሲቪል ቅሬታ ሰሚ ቦርድ፣ እንዲሁም ለግዛቱ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። በተጨማሪም ጠበቃ ማነጋገር ሊፈልጉ ይችላሉ።

**ህዝባዊ እምቢተኝነት ለማቀድ ብፈልግስ?**

ህዝባዊ እምቢተኝነት የተወሰኑ ህጎችን ለመከተል አለመቀበልን በንቃት ተቃውሞ ማሳየት ነው። ከመጀመርዎ በፊት መብቶችዎን ማወቅዎን ያረጋግጡ። ህዝባዊ እምቢተኝነት የሚያስከትላቸውን ተግባራዊ ውጤቶች እና በእስር ቤት የሚቆዩበትን ጊዜ ለመቀነስ መውሰድ ስለሚችሏቸው እርምጃዎች ግንዛቤ ይኑርዎት።

**በእኔ የኮሌጅ ግቢ ውስጥ ለሚደረግ ተቃውሞ የተለዩ ደንቦች አሉ?**

በአጠቃላይ፣ በኮሌጅ ግቢዎ ውስጥ የሚፈቀዱ ንግግሮች ላይ የመሳተፍ መብት አለዎት፤ ይህም የሚሆነው የእርስዎ አገላለጽ የሚከተሉትን የሚያሟላ ከሆነ ነው፦ (1) በግቢው ውስጥ ለሕዝብ ክፍት በሆነ ቦታ ከሆነ፤ (2) ትምህርትን ወይም የትምህርት ቤቱን ሌሎች መሠረታዊ ተግባራት በከፍተኛ ሁኔታ የማያስተጓጉል ከሆነ፤ እና (3) በትምህርት ቤትዎ የተቀመጡትን የ"ጊዜ፣ ቦታ እና ሥርዓት" ደንቦችን የሚያከብር ከሆነ።